የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፴፩
አዲስ አበባ—ጥር ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 31
ADDIS ABABA–4th February, 2003

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፬/፲፱፻፺፭ ዓ·ም

ለኢነርጂ አቅርቦት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር የተገኘው ብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ...................................................... ገጽ ፪ሺ፹፩

## CONTENTS

Proclamation No. 314/2003

International Development Association Credit Agreement for Financing Energy Access Project Ratification Proclamation ........................ Page 2081

### አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፬/፲፱፻፺፭

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለኢነርጂ አቅርቦት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ኤስ·ዲ·አር· ፩፻፬ሚሊዮን ፱፻ሺህ (አንድ መቶ አራት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሺህ ኤስ·ዲ·አር) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ·ኤ·አ· ሴፕቴምበር ፳፮ ቀን ፪ሺ፪ በዋሽንግተን ዲ·ሲ የተፈረመ በመሆኑ፣

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለም አቀፍ ውሎች ተፈፃሚ ከመሆናቸው በፊት መጽደቅ ስላለባቸው፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለኢነርጂ አቅርቦት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር የተገኘው ብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፬/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### PROCLAMATION NO. 314/2003

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE CREDIT AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

WHEREAS, a Credit Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Credit amount of SDR 104,900,000 (one hundred four million nine hundred thousand) Special Drawing Rights for financing Energy Access Project, was signed in Washington D.C. on the 26th day of September, 2002;

WHEREAS, basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Credit Agreement at its session held on the 4th day of February, 2003;

NOW, THEREFORE, in accordance with Sub-Articles (1) and (12) of Article 55 of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*
   This Proclamation may be cited as the "International Development Association Credit Agreement for Financing Energy Access Project Ratification Proclamation No. 314/2003."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ·ኤ·አ· ሴፕቴምበር ፳፮ ቀን ፪ሺ፪ በዋሽንግተን ዲ·ሲ· የተፈረመው ቁጥር ፫ሺ፯፻፲፪ ኢ·ት· የብድር ስምምነት ነው።

፫· <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ኤስ·ዲ·አር· ፩፻፬ሚሊዮን ፱፻ሺህ (አንድ መቶ አራት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሺህ ኤስ·ዲ·አር·) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከጥር ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation "Credit Agreement" means the Credit Agreement Number 3712 ET signed in Washington D.C. on the 26th day of September, 2002, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association.

3. *Power of the Minister of Finance and Economic Development*

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit amount of SDR 104,900,000 (one hundred four million nine hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Credit Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 4th day of February, 2003.

Done at Addis Ababa, this 4th day of February, 2003.

GIRMA WOLDE GIORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE